የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 35
ADDIS ABABA–4th July, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፯/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ወደ ውጭ አገር በሚላክ ቡና ላይ ስለሚከፈል ታክስ የወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፱፻፮

## CONTENTS

Proclamation No. 287/2002
Tax on Coffee Exported from Ethiopia (Amendment) Proclamation ........................................ Page1906

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፯/፲፱፻፺፬
### ወደ ውጭ አገር በሚላክ ቡና ላይ ስለሚከፈል ታክስ የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ወደ ውጭ አገር በሚላክ ቡና ላይ ስለሚከፈል ታክስ የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ "ወደ ውጭ አገር በሚላክ ቡና ላይ ስለሚከፈለው ታክስ የወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፯/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ማሻሻያ</u>
ወደ ውጭ አገር በሚላክ ቡና ላይ ስለሚከፈል ታክስ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፱/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤
"፬· የታክሱ ማስከፈያ ልክ ፮·፭ ፐርሰንት (ስድስት ነጥብ አምስት በመቶ) የነበረው ዜሮ ይሆናል።"

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤
«፰· <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣን</u>
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወደ ውጭ አገር የሚላከው ቡና መጠን እና የቡና ዋጋ ሲሻሻል የታክሱን ማስከፈያ ልክ አቅርቦ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያስወስናል።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### *PROCLAMATION No. 287/2002*
### *A PROCLAMATION TO AMEND THE PAYMENT OF TAX ON COFFEE EXPORTED FROM ETHIOPIA PROCLAMATION*

WHEREAS, it has become necessary to amend the Tax on coffee exported from Ethiopia Proclamation;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Tax on Coffee Exported from Ethiopia (Amendment) Proclamation No. 287/2002".

2. *Amendment*
Tax on Coffee Exported from Ethiopia Proclamation No. 99/1998 is hereby amended as follows:
1) Article 4 of the proclamation is deleted and replaced by the following new Article 4.
"4. the rate of the Tax which has been 6.5% (six and point five per cent) shall be zero".
2) Article 8 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 8:
"8. power of the Council of Ministers
Where the Council of Ministers is satisfied that the amount of coffee to be exported and the international price for coffee has improved it may submit, the rate of tax to be levied on export coffee, to be approved by the House of Peoples' Representatives."

3. *Effective Date*
This Proclamation shall come into force as of the 4th day of July, 2002.

Done at Addis Ababa, this 4th day of July, 2002.

*GIRMA WOLDE GIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001